# በኢትዮጵያ የጋራ መረዳጃ ማህበር
# የዳላስ ፎርትወርዝ ኢትዮጵያውያን እድር

## ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 001/08

በኢትዮጵያ የጋራ መረዳጃ ማህበር የዳላስ ፎርትዎርዝ ኢትዮጵያውያን እድር አባላት ጠቅላላ ጉባኤ በደንቡ አንቀጽ 22 መሰረት በዲሴንበር 9 ቀን 2008 ጠቅላላ የአባላት ስብሰባ አድርጎ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የደንብ ማሻሻያ አውጥቷል። ይህ ማሻሻያ ደንብ የዋናው የእድር ደንብ አካል በመሆን ሙሉበሙሉ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

ማሻሻያ ደንብ፡

1.1 አንድ የእድሩ አባል በእድር አባልነት ለ 3 አመታት ከቆየ በኋላ ወደ ሌላ የአሜሪካ ግዛት ከተማ ቀይሮ ቢሄድ፡ እና በእድሩ አባልነት ግን መቀጠል ፍላጎቱ ከሆነ፡ የእድሩን መደበኛ መዋጮ በወቅቱ በመክፈል በአባልነት ሊቀጥል ይችላል።

1.2 ወላጆች ከ 18 አመት በላይ የሆኑ እና በጤና ጉድለት መስራት የማይችሉ (disable) የሆኑ ልጆቻቸውን በስራቸው ጥገኛ አድርገው በእድር አባልነት ሊያስመዘግቡ ይችላሉ።

1.3 አንድ የእድር አባል ቢያገባ/ብታገባ ወይንም ልጅ ቢወልዱ አዲሱን የቤተሰብ አባል በእድር አባልነት የማስመዝገብ ሃላፊነት ይኖርባቸዋል። ተጨማሪ ክፍያም ካለ በሰአቱ ማጠናቀቅ እና አዲሱን የቤተሰብ አባል የእድር አባል የማድረግ ሀላፊነት የቤተሰቡ ይሆናል።

1.4 ከ 3/9/09 ጀምሮ ማንኛውም አዲስ የእድር አባል የማመልከቻ ክፍያ $25.00 ዶላር ይከፍላል።

## ማሻሻያ ደንብ ቁጥር 002/09

በኢትዮጵያ የጋራ መረዳጃ ማህበር የዳላስ ፎርትዎርዝ ኢትዮጵያውያን እድር አባላት ጠቅላላ ጉባኤ በደንቡ አንቀጽ 22 መሰረት ኦገስት 11 ቀን 2009 ጠቅላላ የአባላት ስብሰባ አድርጎ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የደንብ ማሻሻያ አውጥቷል። ይህ ማሻሻያ ደንብ የዋናው የእድር ደንብ አካል በመሆን ሙሉበሙሉ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

2.1 ማንኛውም የእድሩ አባልም ሆነ አዲስ የሚመዘገብ አባል እድሩን ለማጠናከር ከመደበኛው አመታዊ ክፍያ ውጭ በእንድ አመት ውስጥ

ተጠናቆ ይሚከፈል የአንድ ግዜ ብቻ ክፍያ $200.00 (ሁለት መቶ) ዶላር ይከፍላል።

2.2 በእድሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 6.5 ላይ ማሻሻያ ተደርጓል። በዚህም መሰረት ማንኛውም የእድሩ አዲስ ተመዝጋቢ አባል እድሩ የሚሰጠውን ጥቅም ሊያገኝ የሚችለው ወይንም የእድሩ ተጠቃሚ የሚሆነው በእድሩ አባልነት ተመዝግቦ ክፍያ ካደረገበት ከስድስት ወር የመቆያ ግዜ በኋላ ነው።

2.3 በእድሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ የእድሩ አባላት የመገኘት ሃላፊነት ያለባቸው ሲሆን በስራም ሆነ በሌላ ጉዳይ በአካል መገኘይ ያልቻለ የእድር አባል የእድሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8.5 በሚያዘው መሰረት ሌላ ወደ ስብሰባ የሚመጣ የእድሩ አባልን ፈልጎ የምርጫ መብቱን በመስጠት (proxy voting) እንዲወክል ይጠበቅበታል። ይህንን ሳያደርግ የቀረ አባል $25.00 ዶልር ቅጣት ለእድሩ ይከፍላለል።